# ወዴት ይሆን ጉዞው?



ከአሳማው ከጅቡ ከተናካሽ ዉሻው፣
ከርሃብ ከርዛት ከጥም ከበሽታው፣
ከእናት ከአባት ገዳይ ከሞትም መሸሻው፣
የሱባኤ ገዳም የት ነው መሸሸጊያው፣
በራፊ ተዛዝሎ ወዴት ይሆን ጉዞው?

በቦንብ በጥይቱ እናት አባት አጥተው፣
እስርና ስደት ወንድም እት ነጥቋቸው፣
በርሃብ በበሽታ ዘመድ አልቆባቸው፣
ጉዞ የጀመሩት እንደዚህ ተዛዝለው፣
ማንን ለመሸሽ ነው? ወዴት ለመሄድ ነው?

አገልግል ሳይዙ ኮዳም ሳይኖራቸው፣
ከንፈራቸው ደርቆ ተሰልቦ አንጀታቸው፣
ሐዘን በዝቶባቸው ደንዝዞ አእምሯቸው፣
ቀኑ እንደጨለማ ጥቅጥቅ ብሎባቸው፣
የት እየሄዱ ነው እርስ በርስ ተዛዝለው?

ከሁለት ከሶስት ከፍ ሳይል እድሜቸው፣
አይናቸው ጎድጉዶ ለትልቶ ቆዳቸው፣
ልባቸው ተክዞ ተቆርጦ አንጀታቸው፣
በጨርቅ ተዛዝሎ ወዴት ይሆን ጉዞው?

አንከሊስ ኩፍኙን ጉንፋን እየሳሉ፣
በወባ ተነድፈው እየተቃጠሉ፣
ጉልበት ተብረክርኮ ደፋ ቀና እያሉ፣
መከራን ለመሸሽ ጉዞ ቢጀምሩ፣
ምን ያህል ርቀው ዘልቀው ይሄዳሉ?

ከአሳማው ከጅቡ ከተናካሽ ዉሻው፣
ከርሃብ ከርዛት ከጥም ከበሽታው፣
ከእናት ከአባት ገዳይ ከሞትም መሸሻው፣
የሱባኤ ገዳም የት ነው መሸሸጊያው፣
በራፊ ተዛዝሎ ወዴት ይሆን ጉዞው?

አሳምሮ ፈጥሮ ቶሎ ያፈረሰው፣
እድገቱን ሲጀምር እንቅፋት የመታው፣
ጋሬጣ አሚካላ እሾሁ እሚወጋው፣
ደም-የጎረሰ መግል ከቁስል እሚፈሰው፣
ጫማ አይቶ እማያውቀው ጎስቋላው እግራቸው፣
ከቅዬ አስነስቶ የት ነው እሚያደርሳቸው?

አቅሙ ልቡ ኖሮት በድንብ ላስተዋለው፣
ገጥ በገጥ አንብቦ መልእክቱን ላገኘው፣
ምን መዝግቦ ይሆን ጨቅላው አእምሯቸው፣
እድገቱን ሳይጨርስ ሰቆቃ የዋጠው።

ለስልጣን ለገንዘብ ህይወት ባጠፋነው፣
ለቀሪ አለም ብለን ወንጀል በሰራነው፣
ባዳ እያገለገልን እነሱን በካድነው፣
ህሊናን በሐራጅ ለከርስ በሸጥነው፣
እጣ ፈንታቸውን በጣም ባከፋነው፣
ተስፋ እድላቸውን እጅግ ባጨለምነው፣
ተሰፍሮ ያልቅ ይሆን ሐዘን ትካዜአቸው?

እንዴት ያዝኑ ይሆን ይከፋ ልባቸው!
እነሱ ከመንገድ ጎዳና ዳር ፈሰው፣
በርሃብ ጦስ ሲያልቁ ሳይደርቅ እትብታቸው፣
ከአፋቸው ሞልቅቀን እየዋጥን ባለነው፣
የአገር ሐብት ዘርፈን ከብረን በናጠጥነው፣
ወላጅ አሳጥተን ሜዳ በጣልናቸው።

ከአሳማው ከጅቡ ከተናካሽ ዉሻው፣
ከርሃብ ከርዛት ከጥም ከበሽታው፣
ከእናት ከአባት ገዳይ ከሞትም መሸሻው፣
የሱባኤ ገዳም የት ነው መሸሸጊያው፣
በራፊ ተዛዝሎ ወዴት ይሆን ጉዞው?

እያንጎራጎሩ እያሰሙ ሳግን፣
እያነጋገሩ እያወጉ እግዜርን፣
“ሰውን ሰው በላው በዚህ ክፉ ዘመን፣
ለገንዘብ ጎምዥቶ እምልኮ ስልጣንን፣
ወላጅን ገደለ እማኝ አርጎ ልጅን፤
ልጅንም አጠፋ ጧሪ አሳጣ አሩግን።”

ከአሳማው ከጅቡ ከተናካሽ ዉሻው፣
ከርሃብ ከርዛት ከጥም ከበሽታው፣
ከእናት ከአባት ገዳይ ከሞትም መሸሻው፣
የሱባኤ ገዳም የት ነው መሸሸጊያው፣
በራፊ ተዛዝሎ ወዴት ይሆን ጉዞው?

እያነሱ ይሆን ጥያቄ ቅሬታን፣
ምድር እያጫሩ እያዩ ሰማዩን፣
ብለው በመጠየቅ በለወስታ ጌታን፣
“አምላክ ሆይ አሳዬን እውነት መኖርህን፣
ከችሎት ቁጭ ብለህ በመፍረድ ፍርድህን፣
ወደ አንተ ስንመጣ ተላብሰን ሰቆቃን፣
ወንድምና እህቶች በእራፊ ተዛዝለን።”

ከአሳማው ከጅቡ ከተናካሽ ዉሻው፣
ከርሃብ ከርዛት ከጥም ከበሽታው፣
ከእናት ከአባት ገዳይ ከሞትም መሸሻው፣
የሱባኤ ገዳም የት ነው መሸሸጊያው፣
በራፊ ተዛዝሎ ወዴት ይሆን ጉዞው?

*ተጻፈ ታህሳስ ፩ ቀን ሁለት ሺህ ዓ.ም.*
*በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)*